# ሽግግር፡- ቀጣዩ እርምጃ፡-

## ልጄ ሦስት ዓመት ሲሆነው ምን ይፈጠራል?



**የአካል ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦች የትምህርት ሕግ (IDEA) ክፍል ሐ መሰረት ከጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎቶች ስለመሸጋገር የተዘጋጀ መመሪያ።**

በዋሽንግተን ግዛት የጨቅላነት ጊዜ ትምህርት ክፍል የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግለት፣ የጨቅላ ሕጻናት እና ድክ ድክ የሚሉ ሕጻናት የጨቅላነት ጊዜ ድጋፍፕሮግራም

Washington State Department of
CHILDREN, YOUTH & FAMILIES

# ሽግግር ምንድነው?

ልጅዎ ሦስት ዓመት ሲሆነው፣ የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎቶች ያበቁ እና አዲስ አገልግሎቶች እና ድጋፎች ይዘጋጃሉ። ይህ የለውጥ ሂደት ልጅዎ እና ቤተሰብዎ በሕይወት ዘመናችሁ ሊታለፉባቸው ከምትችሏቸው በርካታ ሽግግሮች አንዱ ነው።

ከልጅዎ ሦስተኛ ዓመት የልደት በዓል ከስድስት እስከ ዘጠኝ ወር ቀደም ብሎ፣ የልጅዎን ወደ ቅድመ ትምህርት ቤት የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ወይም ወደ ሌሎች አስፈላጊ አገልግሎቶች እና ድጋፎች መሸጋገርን አስመልክቶ ከእርስዎ የቤተሰብ መረጃ አስተባባሪ (FRC) እና ከቡድንዎ ጋር በጋራ ይሰራሉ። ቤተሰቦች እና አገልግሎት ሰጪዎች በዚህ ሂደት አብረው በመሆን ወደ ሽግግር ስብሰባ የጋራ ጉዞ ያደርጋሉ።

# የሽግግር ስብሰባ ዓላማው ምንድነው?

በ IFSF ስብሰባ ወቅት፣ እርስዎን በሽግግር ሂደቱ ውስጥ ለመምራት በራስዎ እና በጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎት ሰጪ ቡድንዎ የጽሁፍ

የሽግግር ዕቅድ ይዘጃል።የአካል ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦች የትምህርት ሕግ (IDEA) ክፍል ሐ ከልጅዎ ሦስተኛ ዓመት የልደት በዓል በፊት ለሽግግር በጽሁፍ የተዘጋጀ ዕቅድ እንዲኖር ያስገድዳል።

# ለሽግግር ማቀድ የምን ጀምረው መቼ ነው?

## ከልጅዎ ሦስተኛ ዓመት የልደት በዓል ከስድስት እስከ ዘጠኝ ዓመት ቀደም ብሎ፡-

ለሽግግር ማቀድ ይጀመራል። በሦስት ዓመት ዕድሜ ላይ ለሚደረገው የልጅዎ ሽግግር የእርስዎ FRC በእ ርስዎ እና በትምህርት ቤት ቀጠናዎ ወይም በሌሎች ማህበረሰብ-መር ፕሮግራሞች መካከል ሁኔታዎችን ያመቻቻል።

## ከልጅዎ ሦስተኛ ዓመት የልደት በዓል ቢያንስ ሦስት ወራት ቀደም ብሎ፣ ሽግግር የማቀድ ስብሰባ ይደረ ጋል፡-

የስብሰባው አካል በመሆን ከትምህርት ቤት ቀጠናው ተወካይ ጋር ይገናኛሉ። ልጅዎ ለቅድመ ትምህርት ቤት የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ብቁ መሆን አለመሆኑን ለመወሰን ምን እንደሚከናወን ያብራራሉ።

በትምህርት ቤት ቀጠናው ውሳኔ መሰረት ልጅዎ ለቅድመ ትምህርት ቤት የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ብቁ ሆኖ ከተገኘ፣ በግለሰብ ተኮር የትምህርት ፕሮግ ራም (IEP) አማካኝነት አገልግሎቶች ይሰጣሉ

የቅድመ ትምህርት ቤት የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን ለማግኘት ካልፈለጉ ከትምህርት ቤት ቀጠና ተወካይ ጋር ስብሰባ ለማድረግ ቀጠሮ አይያዝም።

# የሽግግር ዕቅድ ምንድን ነው?

የሽግግር ዕቅድ በልጅዎ ሦስተኛ ዓመት ዕድሜ ላይ ልጅዎ እና ቤተሰብዎ ከጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎቶች ስታልፉ እርስዎ፣ የእርስዎ FRC እና የልጅዎ የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎት ቡድን ሂደቱን እንዴት ሊታግዙ እንደምትችሉ ያሳያል። ዕቅዱ፣ ልጅዎ በአካባቢው ወደሚገኝ የትምህርት ቀጠና የቅድመ-ትምህርት ልዩ የትምህርት ፕሮግራም ወይም ሌሎች ማህበረሰብ-መር አገልግሎቶች በሚሸጋገርበት ጊዜ፣ ወይም የብቁነት ጊዜው በማብቃቱ ድጋፎችን እና አገልግሎቶችን ለቆ በሚወጣበት ጊዜ ምን ዓይነት ድጋፎች፣ እርምጃዎች እና አገልግሎቶች እንደሚያስፈልጉ ይዘረዝራል።

# ቀጣዩ የልጄ ዕድል ምንድን ነው?

## የልጄን የሽግግር ዕቅድ ማዘጋጀት፡-

እርስዎ እና የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎት ቡድንዎ ዕቅዱን ለማዘጋጀት በጋራ ትሰራላችሁ። ቡድኑ፣ እርስዎን፣ የእርስዎን FRC፣ አሁን ከእርስዎ ጋር የሚሰሩ ሰዎችን እና እንዲሳተፉ የሚፈልጓቸውን ሌሎች ሰዎች እና ለወደፊቱ በልጅዎ ጉዳይ ላይ የሚሰሩ ሰዎችን ያካትታል። ቡድኑ በልጅዎ ለውጥ እና ፍላጎቶች ላይ ይሠራል። የሽግግር ዕቅድ ዝግጅቱን FRC ያስተባብራል።

### ልጄ ሦስት ዓመት ካለፈው በኋላ ምን ዓይነት አገልግሎቶች ሊሰጡ ይችላሉ?

ይህ ልጅዎ የቅድመ ትምህርት የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ያስፈልጉታል ወይም አያስፈልጉትም በሚለው ላይ የተመሰረተ ነው። ልጅዎ ለቅድመ ትምህርት የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ብቁ ነው አይደለም የሚለውን የትምህርት ቤት ቀጠናዎ ይወስናል። ልጅዎ ብቁ ከሆነ፣ የተለያዩ የአገልግሎት ስብስቦች ሊዘጋጁ ይችላሉ፣ እነዚህም የማህበረሰብ ፕሮግራም፣ ሄድ ስታርት፣ የጨቅላነት ልጅነት ጊዜ ትምህርት እና እገዛ ፕሮግራም (ECEAP)፣ ወይም ትምህርት ቤት ተኮር፣ የቅድመ ትምህርት ልዩ የትምህርት ፕሮግራም። በግለሰብ ተኮር የትምህርት ፕሮግራም (IEP) በኩል የልዩ ትምህርት እና ተያያዥ አገልግሎቶች ይሰጣሉ። የሽግግር ዕቅድ ስብሰባውን FRC ያስተባብራል። የትምህርት ቤት ቀጠናው የልጅዎን IEP ለማዘጋጀት ስብሰባ ያዘጋጃል።

የእርስዎ FRC ለ IEP ስብሰባ እንዲጠራ ሊጠይቁ ይችላሉ። የመረጡትን ጓደኛ፣ የቤተሰብ አባል ወይም ሌሎች የማህበረሰብ አባላት ለድጋፍ ወደ IEP ስብሰባ ይዘው መምጣት ይችላሉ። የዕድገት ዕክሎች መምሪያ (DDD) የጉዳይ አስተዳዳሪ ካለዎት ወይም ልዩ የጤና እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸው ሕጻናት (CSHCN) አስተባባሪ ካለዎት እነርሱንም ሊጋብዟቸው ይችላሉ። የ IEP ስብሰባ ከልጅዎ ሦስተኛ ዓመት የልደት በዓል በፊት መከናወን አለበት እናም በልጅዎ ሦስተኛ ዓመት የልደት በዓል ላይ IEP በስራ ላይ መዋል አለበት። የ IEP ስብሰባዎች በየዓመቱ ይዘጋጃሉ። ነገር ግን፣ በማንኛውም ጊዜ እርስዎ ወይም የትምህርት ቤቱ ሠራተኞች በልጅዎ ፕሮግራም ላይ ለመወያየት ሲፈልጉ የ IEP ስብሰባ እንዲደረግ መጠየቅ ይችላሉ።

### ልጄ ለቅድመ ትምህርት ቤት ልዩ የትምህርት አገልግሎቶች ብቁ ሆኖ ካልተገኘ ምን ይፈጠራል?

ልጅዎ ለቅድመ ትምህርት ቤት የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ብቁ ካልሆነ፣ ሄድ ስታርትን፣ ECEAPን የመሳሰሉ እና ሌሎች የማህበረሰብ አገልግሎቶችን ጨምሮ ለልጅዎ የተዘጋጁ ሌሎች አማራጮችን ለመለየት የእርስዎ FRC ከእርስዎ ጋር በጋራ ይሰራል።

## በሽግግር ሂደቱ ውስጥ የእኛ ሚና ምንድነው?

### ልጅዎ እና ቤተሰብዎ ሰላማዊ ሽግግር እንዲያደርጉ የሚረዱ ነጥቦች:-

- ለልጅዎ ምን እንደሚፈልጉ በመናገር በስብሰባዎች ላይ መሳተፍ።
- በስብሰባዎች ላይ ማስታወሻዎችን መያዝ።
- የመረጃ ሐብቶችን እና አገልግሎቶችን ማፈላለግ።
- የልጅዎን ተግባራት እና ፍላጎቶችን የሚመዘግቡበት ማስታወሻ ደብተር ማዘጋጀት የልጅዎን የልደት ምስክር ወረቀት፣ የክትባት ማህደሮች፣ የሕክምና ሪፖርቶች፣ ፎቶግራፎች፣ ግምገማዎች፣ ምዘናዎች እና ያለፉ IFSP ዎችን ማካተት። የልጅዎን ፎቶ ማከተትዎ መረጃዎችን እና ፍሬ ነገሮችን ግላዊ ለማድረግ ይረዳል።
- የልጅዎን መብት ለማስጠበቅ ሊረዳዎ የሚችለው ነገር ምንድነው? የልጅዎ የሚያስፈልጋትን/የሚያስፈልገውን ነገር እርስዎ ከማንም በተሻለ ያውቃሉ። ከልጅዎ ምን መጠበቅ እንዳለብዎ ይወቁ እና እነዚያን አገልግሎቶች ለልጅዎ ለማግኘት ከትምህርት ቤት ቀጠናው እና ከ IEP ቡድን ጋር ይስሩ።

## ከሽግግር በኋላ ቀጣይ እርምጃዎቹ ምንድን ናቸው?

በቀጠናዎ ውስጥ የቤተሰብ የድጋፍ ቡድን፣ የአካባቢ የወላጅ መምህራን እና ተማሪዎች ማህበር (PTSA) ወይም የልዩ ትምህርት የወላጆች አማካሪ ምክር ቤት (SEPAC) ስለመኖሩ ይጠይቁ። ማንኛውም ዓይነት ስጋት ካለብዎት ቀጣናው ሊረዳዎት የሚችል የቤተሰብ አገልግሎቶች ባለሙያ፣ የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያ፣ ወይም የትምህርት ቤት የሥነ ልቦና ባለሙያ ያለው ስለመሆኑ ይጠይቁ። ቤተሰብዎ በሽግግር ሂደት ውስጥ በሚጓዝበት ጊዜ እርስዎ፣ እንደ ወላጅ፣ ለራስዎ እንዲሁም ለልጅዎ የድጋፍ አገልግሎቶችን በማግኘት ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ።

## ሌላ ልናውቀው የሚገባን ምን ዓይነት መረጃ አለ?

በአሁኑ ወቅት ልጅዎ ከ DDD አገልግሎቶችን ለማግኘት ብቁ ከሆነ፣ ልጅዎ አራት ዓመት ዕድሜ ላይ ከመድረሱ በፊት ለአገልግሎቶች ያለው ብቁነት ዳግም መታየት እና መወሰን አለበት። በዚህ የሽግግር ሂደት ወቅት ለ DDD የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎት ምዘናዎችን፣ የሽግግር መረጃዎችን እና የትምህርት ቤት ቀጠናውን የግምገማ ሪፖርት ማጋራትዎ አስፈላጊ ነው። **ይህንን መረጃ ለ DDD ለመስጠት የሚሰጡት ፈቃድ በሽግግር ዕቅድ ስብሰባ ላይ ከትምህርት ቤቱ ቀጠና ሊገኝ ይችላል። የልጅዎን ቀጣይ የብቁነት ሁኔታ ለመወሰን መረጃ ካልተገኘ፣** ልጅዎ አራት አመት ሲሞላው የ DDD አገልግሎት መሰጠት ያቆማል።

# ለተጨማሪ ዕርዳታ ወይም ለበለጠ መረጃ ወዴት መሄድእችላለሁ?



የጨቅላነት ጊዜ ትምህርት ክፍል፣ የጨቅላ ሕጻናት እና ድክ ድክ የሚሉ ሕጻናት የጨቅላነት ጊዜ ድጋፍ (ESIT) ፕሮግራም ግዛት አቀፉን የ IDEA ክፍል ሐ የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎቶች ይመራል።

(360) 725-3500

**www.dcyf.wa.gov**

ለተጨማሪ መረጃ እና ወደ ቤተሰብ መረጃ አስተዳደር ለመመራት (FRC) በሚከተለው አድራሻ ይጠይቁ፡-Help Me Grow Washington በእርስዎ አካባቢ የሚገኝን FRC ስም ለማግኘት።

1-800-322-2588

የዋሽንግተን ግዛት የአባቶች ትስስር በኪንደሪንግ ሴንተር። ልዩ ፍላጎት ያላቸው ሕጻናት ላሏቸው ወንዶች እና ቤተሰቦቻቸው በሙሉ የድጋፍ አገልግሎት ይሰጣል፣ እንዲሁም ድጋፍ እና መረጃ እንዲያገኙ ይሟገታል።

(425) 653-4286

**www.fathersnetwork.org**

PAVE አካል ጉዳት ላለባቸው ሕጻናት ቤተሰቦች ከውልደት አንስቶ እስከ ጉልምስና ድረስ እገዛ የሚሰጥ ግዛት አቀፍ የወላጅ ሥልጠና እአና መረጃ ማዕከል ነው።

1-800-572-7368 (800-5 PARENT)

**www.wapave.org**

የዋሽንግተን ግዛት የወላጅ ለወላጅ ፕሮግራም ግዛት አቀፍ የወላጆች ትስስር ሲሆን የአካል ጉዳት ወይም የዕድገት መዘግየት ላለባቸው ሕጻናት ወላጆች የስሜት ድጋፍ እና መረጃ ይሰጣል።

1-800-821-5927

**www.arcwa.org/parent-to-parent**

ዘ አርክ ኦፍ ዋሽንግተን ስቴት የዕድገት ዕክል ላለባቸው ግለሶች እና ቤተሰቦቻቸው የትምህርት፣ የጤና፣ ራስን-መቻል፣ ራስን መግለጽ፣ መደባለቅ፣ እና ምርጫን ማስጠበቅን ያበረታታል።

1-888-754-8798

**www.arcwa.org**

የሕዝብ መመሪያ ተቆጣጣሪ ቢሮ (Office of Superintendent of Public Instruction) የልዩ ትምህርት እና ተያያዥ አገልግሎቶችን ለሚያገኙ ሕጻናት ወላጆች ጠቃሚ መረጃዎችን **www.K12.wa.us/SpecialEd/Families/default.aspx** ላይ አካቷል።


**The Washington State Department of Children, Youth & Families Early Support for Infants and Toddlers**

PO Box 40970
Olympia WA 98504-0970
ፋክስ: (360) 725-4925
ድምጽ: (360) 725-3500
**www.dcyf.wa.gov/services/child-development-supports/esit**


*በሁሉም ፕሮግራሞች እና ተግባራት መድልዎ የተከለከለ ነው። ማንኛውም ሰው በዘር፣ በቀለም፣ በሐይማኖት፣ በእምነት፣ በመጣበት አገር፣ በጾታ፣ በዕድሜ ወይም በአካል ጉዳት መድልዎ ሊደረግበት አይገባም።*

*የዚህን ሰነድ ቅጂዎች በተለዋጭ ቅርጸት ወይም ቋንቋ ከፈለጉ ፣ እባክዎ ያነጋግሩ የ DCYF የሰራተኛ ግንኙነቶች (1-800-723-4831 | 360-902-8060 ፣ **ConstRelations@dcyf.wa.gov**).*


DCYF PUBLICATION FS_0004 AM | DEL 11-013 AM (01-2020)